# ዜና መጽሔት

ቅጽ 2 ቁጥር 3 የካቲት 2013 ዓ.ም









## የሆቴልና ቱሪዝም ስራ ማሰልጠኛ ማዕከል በተለያዩ የትምህርት ዘርፍ ያሰለጠናቸውን 425 ተማሪዎችን አስመረቀ።

በምረቃ ስነ-ስርዓቱ ላይ የተገኙት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ዶክተር ሂሩት ካሳው ባስተላለፉት መልዕክት “አስቸጋሪውን የኮቪድ-19 ወቅት በማለፍ ለምርቃት በመብቃታችሁ ተማሪዎችን እና የተቋሙ ሰራተኞች እንኳን ደስ አላችሁ” ብለዋል።

ተመራቂዎች ከባለሙያነት ባለፈ የአገር አምባሳደሮች በመሆናቸው በሃላፊነት መስራት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

ቱሪዝም ለአገር ኢኮኖሚ ያለውን ፋይዳ ተግባራዊ ለማድረግ ከተመራቂዎች ብዙ ስለሚጠበቅ በትጋት መስራት እንዳለባቸው ተናግረዋል።

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ ፕሮፌሰር አፍወርቅ ካሱ በበኩላቸው ትምህርትን በተገቢው መንገድ ተግባራዊ ማድረግ ከተመራቂ ተማሪዎች እንደሚጠበቅ ተናግረዋል።

“መንግስት እና ህዝብ የሰጣችሁን ሀላፊነት በመወጣት ከዘርፉ የሚገኘውን ፋይዳ አገራችን እንድታገኝ የዜግነት ግዴታችሁን ተወጡ” ሲሉ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

የሆቴልና ቱሪዝም ስራ ማሰልጠኛ ማዕከል ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ አስቴር ዳዊት የዘንድሮ ተመራቂዎች ከፍተኛ ቁጥርና ውጤት ያላቸው ሴቶች መሆናቸውን ገልጸዋል።

ተመራቂዎቹ የኮቪድ-19 ፈተናን ተጋፍጠው ለዚህ ስኬት መብቃታቸው የሚያስመሰግናቸው እንደሆነ ተናግረዋል።



**በኮምኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ**




## የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ

በ1962 ዓ.ም የተመሰረተ ሲሆን ከአ.አ. በ400 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በባየባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ

በ1962 ዓ.ም የተመሰረተ ሲሆን ከአ.አ. በ400 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በባሌ ዞን ውስጥ ይገኛል፡፡ ስፋቱ ወደ 2200k.m2 የሚደርስ ሲሆን ከሰሜን ወደ ደቡብ 74 ኪ.ሜ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ ደግሞ 53 ኪ.ሜትር ይሰፋል፡፡ ፓርኩ ከባህር ወለል በላይ ከ1450 እስከ 4377 ሜትር ባለ ልዩነት ውስጥ የሚገኙ አካባቢዎችን ያካትታል፡፡ 4377 ሜትር የሚረዝመው እና ከኢትዮጵያ በከፍታው ሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው የቱሉ ዲምቱ ተራራን ጨምሮ የአፍሮ አልፓይን ከፍተኛ ቦታዎች በዚህ ፓርክ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ የባሌ ተራሮች ከፍተኛ አካባቢ በተለያየ መንገድ የተፈጠሩ ሀይቆች፤ እርጥበት አዘል መሬቶች የያዘ ነው፡፡

ፓርኩ ከ1600 በላይ የሚሆኑ ልዩ ልዩ ዓይነት ዕፀዋቶች፣ 78 ዓይነት አጥቢ የዱር እንስሳትና ወደ 200 የሚጠጉ አእዋፋት በፓርኩ ተጠልለው ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም መካከል 32 ዓይነት ዕፀዋቶች፣ 31 የሚጠጉ ብርቅዬና ድንቅዬ የዱር እንስሳትና ወደ ስድስት የሚጠጉ ዕፀዋት በብሔራዊ ፓርኩ ካልሆነ በስተቀር በሌላው ዓለም ፈጽሞ አይገኙም፡፡ በባሌ ተራሮች ብሄራዊ ፓርክ ክልል ውስጥ ከሚገኙ 78 የሚደርሱ አጥቢ የዱር እንሰሳት 17 የሚሆኑት በኢትዮጵያ ብቻ ከሚገኙት ብርቅዬ እንሰሳት መካከል ቀይ ቀበሮ፣ኒያላ ፣ አጋዘን እና ሌሎችም ይጠቀሳሉ፡፡

ከዚህ ባሻገር ለሳይንስና ኢኮሎጂ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው በደረታቸው የሚሳቡ ልዩ ልዩ እንስሳትና መንቆረረቶችን ፓርኩ አቅፎ ይዟል፡፡ ቡናና በኢትዮጵያ ውስጥ ለባህል መድኃኒትነት የሚውሉ 40 ከመቶ ዕፀዋቶችም ይገኙበታል፡፡ በእፅዋት እና በእንሰሳት ብዝሃ ህይወት መበልፀግ ደረጃ ፓርኩ ከዓለም 34ኛ ከአፍሪካ ደግሞ 12ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጧል፡፡

የባሌብሄራዊ ፓርክ በ “Bird lite International” በዓለም ከሚገኙ አስፈላጊ የአዕዋፍ መኖሪያ በታዎች ጎራ ተመድቧል፡፡

በፓርኩ ከ280 በላይ የአዕዋፍ ዝርያዎች የሚኖሩ ሲሆን ሰባቱ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ናቸው፡፡

እንደ ዓለም አቀፍ የወፎች ድርጅት ሪፖርት ከሆነ የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ የአፍሪካ አራተኛው ‹‹በርዲንግ ሳይት›› ተብሎ ተመዝግቧል፡፡ በባሌ ብሔራዊ ፓርክ ዋቢ ሸበሌ፣ ዌብ፣ ዱማል፣ ያዶት እና ወልመል የተሰኙ ወንዞች ይፈሳሉ፡፡











## የቱሪዝም ዘርፍ ሁለተኛ ዓመት ሰልጣኞች የዓለም ቅርስ የሆነውን ጢያ ትክል ድንጋይን ጎበኙ

የጢያ ትክል ድንጋይ ከአዲስ አበባ ወደ ቡታጂራ በሚወስደው መንገድ 88 ኪሎ ሜትር ርቃ ከምትገኘው ሶዶ ወረዳ በጢያ ከተማ ይገኛል። ጢያ በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጧ ከምድር ሰቅ (ኢክዌተር) 8026′ ሰሜን 38037′ ምሥራቅ እንደሆነ የዩኔስኮ ዘገባዎች ያመለክታሉ። የጢያ ታሪካዊ ድንጋይ በቁጥር 51 የሚደርሱ ሲሆን ልዩ ልዩ ቅርጾች ምስሎች ያሉባቸው ናቸው። ሁሉም ድንጋዮች የተለያየ ርዝመት፣ ስፋትና ውፍረት አላቸው።

በአብዛኛው ከታች ሰፋ ብለው ወደ ላይ እየሾጠጡ የሚሄዱ ናቸው። የአንዳንዶቹ ትክል ድንጋዮች ቁመትም ከ1-5 ሜትር እንደሚረዝም የአርኪዮሎጂ አጥኚ ሥራዎች ያመለክታሉ። በድንጋዮቹ ላይ የተቀረጹት ምስሎችም የጎራዴ ወይም የሰይፍ ወይም የጩቤ፣ የጦር፣ የትራስ እንጨት፣ ክብ ዳቦ ወይም ፀሐይ መሰል ቅርጾች፣ የግማሽ ጨረቃ ምስሎች እጆቹን ወደላይ የዘረጋ ሰው ክንዶች ናቸው።

በቅድመ ታሪክ ይኖሩ የነበሩት ኢትዮጵያውያን ድንጋዮቹን ለምን እንደተከሏቸው ባይታወቅም ትልቅ የጦር መሪዎች፣ ገዥዎችና ታላላቅ ሰዎች የተቀበሩባቸው ሥፍራዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገመታል። ትክል ድንጋዮቹ ከ800 ዓመት በፊት እንደተተከሉ ይገምታሉ። የፈረንሳይ አርኪዮሎጂ ባለሙያዎች መረጃ እንደሚያመለክተው የጢያ ትክል ድንጋይ ባለበት ቦታ ዕድሜያቸው ከ18-30 የሚገመቱ ብዙ ወጣቶች በአንድ ላይ የተቀበሩበት ሥፍራ ነው።

ጢያ ትክል ድንጋይ እ.ኤ.አ ከ1980 ጀምሮ በዓለም የቅርስ መዝገብ ሰፍሮ የሚገኝ ቦታ ነ ው

## የተለያዩ መመሪያዎች እየተሰሩ መሆናቸው ተገለጸ

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማስልጠኛ ማዕከል የህግ ክፍል ለተቋሙ ሊረዱ የሚችሉ የተለያዩ መመሪያዎችን እያዘጋጀ መሆኑ ተገለጸ።

በተቋሙ እንደ መልካም አስተዳደር ችግር እየታዩ የመጡ ጉዳዮችን ሊፈታ የሚችል መመሪያ እያዘጋጁ እንደሆነ አቶ ግርማ ገመቹ ተናገሩ።

የህግ ክፍሉን ጨምሮ ከተለያዩ የስራ ክፍሎች የተውጣጡ 13 አባላት ያሉት ቡድን በማዋቀር ራሳቸውን በሶስት ዝቅተኛ ቡድን በማከፋፈል በተለያዩ ዘርፎች ማለትም በሬጅስትራር፣ የማታና አጫጭር፣ ምርምር ክፍሎችንና የስነምግባር መመሪያዎችን እያዘጋጁ እንደሆነ የህግ ክፍሉ ኃላፊ ተናግረዋል።

ቡድኑ ያለበትን ደረጃና ሂደቱን ለመከታተል በቦታው የተገኙት የተቋሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ እንደተናገሩት ቡድኑ እየሰራ ያለው ስራ የሚበረታታ መሆኑንና ተቋሙ ውስጥ ለሚነሱ ችግሮችም መፍትሔ የሚሆኑ መመሪያዎች ሊዘጋጁ እንደሚችሉ ተናግረዋል። ቡድኑ ይዞ የሚመጣውም መመሪያ በተለያዩ አካላት በመታየት ወደስራ እስከሚገባ ድረስ ተስፋ ሳይቆረጥ በጥንካሬ መሰራት እንዳለበት አቶ ገዛኸኝ አሳስበዋል።



**የማዜ ብሔራዊ ፓርክ**

የማዜ ብሔራዊ ፓርክ ከአዲስ አበባ 468 ኪ.ሜትር ከሐዋሳ ደግሞ 248 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በጋሞ ጎፋ ዞን ይገኛል፡፡ ፓርኩ 220 ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት አለው፡፡ በ1997 ዓ.ም በህዝቡ ጥያቄና በክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ደጋፊነት በብሄራዊ ፓርክነት የተከለለው ማዜ ተፈጥሯዊ ሃብቱ ከመልክዓ ምድራዊ አቀማመጡ ጋር ተዳምሮ በአጭር ጊዜ ቀልብ ሳቢ መዳረሻ ከሆኑ ስፍራዎች አንዱ ሆኗል፡፡

የማዜ አየር ንብረት ሶስት ዓይነት መልኮች ሲኖሩት ከሰኔ እስከ ነሐሴ ቀዝቃዛ ፤ ከመጋቢት እስከ መስከረም ዝናብ የሚያገኝበት ወቅት ሲሆን ከህዳር እስከ የካቲት ያለው ወቅት የሙቀት ሰዓት ነው፡፡

ፓርኩ ስያሜውን ያገኘው ፓርኩን አቋርጦ ከሚፈሰው ከትልቁ የማዜ ወንዝ ነው፡፡ ማዜን ውበት ያጎናጸፉት እነዚህ ወንዞች ዳርቻቸው በደን የተሸፈነና በፓርኩ የሚያልፉ በርካታ ወንዞች መድረሻቸው ኦሞ ወንዝ ነው፡፡

በሳቫና ሳር የተሸፈነው የማዜ ብሔራዊ ፓርክ በተለይም ዝናብ በሚያገኝበት ወቅት ለምለምና አረንጓዴ መልክ ሲኖረው ለእይታም በእጅጉ የሚስብ ነው፡፡ ማዜን የተለየ ከሚያደርጉት መገለጫዎች አንዱ በውስጡ የሚኖሩ የዱር እንስሳትን በቀላሉ የሚመለከቱበት ፓርክ መሆኑ ነው፡፡

ማዜ ላይ በተደረገው ጥናት እስከአሁን 39 መካከለኛና አጥቢ እንስሳት ዝርያዎች እና 196 የአእዋፍ ዝርያዎች ተመዝግበዋል፡፡ በዋናነት የስዋይንስ ቆርኪ፣ ፌቆ፣ በሆር፣ ጎሽ፣ ከርከሮ፣ ድፈርሳ፣ ድኩላ፣ የዱር አሳማ፣ ትልቁ አጋዘን ዝንጀሮ፣ ጦጣ፣ ጉሬዛ፣ አንበሳ፣ የዱር ድመት ወዘተ ይገኙበታል፡፡

በሰንሰለታማ እና በድንቅ አፈጣጠር የተዘረጉ ተራራዎች የከበቡት ማዜ በርካታ አስደናቂ መስህቦችን አቅፎ የያዘ መዳረሻ ነው፡፡ ቢልቦ ወይም ሀቦ ፍል ውሃ በሚል የሚጠራው የተፈጥሮ ፍል ውሃ በማዜ የላይኛው ተፋሰስ የሚገኝ ሲሆን በፈዋሽነቱ ይታወቃል፡፡

ወንጂያ ትክል ድንጋይ ዋሻ ከ300 ያላነሰ ህዝብ መያዝ የሚችል ዋሻ ሲሆን ማዜ ከያዛቸው መዳረሻዎች መካከል የሚጠቀሱት ናቸው፡፡



# አዞ ገበያ

የአዞ ገበያ ከአርባ ምንጭ ከተማ በ10ኪ.ሜ ርቀት በጫሞ ሐይቅ ላይ የሚገኝ መስህብ ነው፡፡ "አዞ ገበያ" አዞ ገበያ የሚለው ስያሜ የተገኘው በርካታ ቁጥር ያላቸው አዞዎች በአንድነት በአሸዋማው የጫሞ ሃይቅ ዳረቻ ተሰብስበው ፀሐይ የሚሞቁበት ቦታ ከመሆኑ በተጨማሪ ወፎች ከአዞዎች ጥርስ ስጋ የሚነቅሉበትና የሚበሉበት ሁኔታን የሚገልጽ ስም ነው፡፡ በርካታ ቁጥር ያላቸው አዞዎች፣ ጉማሬዎችና አእዋፋት በዚህ ቦታ አንድ ላይ በሠላም አብረው ሲገኙ ማየት የጎብኚዎችን ቀልብ ይስባል ፡፡

የማሰልጠኛ ማዕከሉ የቱር ኦፕሬሽን ሱፐርቪዥን፣ ቱር ጋይድና ቱሪዝም ማኔጅመንት ሰልጣኞች ነገ ሀገራችንን ከዘርፉ ተጠቃሚ ለማድረግ መሠረት





የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል በቱሪዝም ማኔጅመንት፣ ቱር ኦፕሬሽን ሱፐርቪዥንና ቱር ጋይድ እያሰለጠናቸው የሚገኙ ሰልጣኞች በደቡብ ኢትዮጵያ በሚገኙ ታሪካዊ፣ ባህላዊና ሰው ሰራሽ የቱሪስት መደረሻ ቦታዎች ላይ በክፍል ውስጥ በንድፈ ሃሳብ የሰለጠኑትን የመስክ የተግባር ስልጠና እያሰለጠነ ነው፡፡

የመስክ የተግባር ስልጠናው አንድ አስጎብኝ እንግዳን ለማስጎብኘት ምን ዓይነት ዝግጅት ማድረግ እንዳለበት፣ የቋንቋ ክህሎት፣ ስለሚያስጎበኙት አካበቢና ቅርስ ያላቸውን ግንዛቤ ለማሻሻል፣ በጉዞ ወቅት ሊገጥሙ የሚችሉ ችግሮችና እንዴት መፍታት እንደሚገባ፣ የጉብኝት መርሐ ግብር ዝግጅትና የሰዓት አጠቃቀም እና የቱሪዝም መዳረሻዎችን ማስተዋወቅ የሚሉ መሠረታዊ ስልጠናዎች የሚያገኙበት መሆኑን የመስክ ስልጠናውን ከሚመሩ አሰልጣኞች መካከል መምህር አለምነህ መርሻ ገልጸዋል፡፡

ሰልጣኞችም በበኩላቸው በቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች ላይ ተገኝተው ስልጠናውን በመከታተላቸው ለወደፊት በዘርፉ ተሰማርተው የሀገራችንን ቱሪዝም ለማሳደግ ለሚያደርጉት አስተዋጽኦ ትልቅ መሰረት እንደሚሆናቸው ገልጸዋል፡፡

የመስክ የተግባር ስልጠናው የካቲት 01/2013 ዓ.ም የተጀመረ እስከ የካቲት 8/2013 ዓ.ም ድረስ ጢያ ተክል ድንጋይ፣ መልካ ቁንጡሬ መካነ ቅርስ፣ ማዜ ብሔራዊ ፓርክን ጨምሮ የተለያዩ ቦታዎችን ጎብኝተዋል፡፡

## በባለሙያዎች መካከል የእርስ በእርስ ስልጠና ተካሄደ

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል የቱሪዝም መምህራንና በደብረብርሃን ዩንቨርሲቲ ቱሪዝም መምህራን መካከል የጋራ የእርስ በእርስ ስልጠና ተካሄደ፡፡

ከዚህ በፊት ከደብረብርሃን ዩንቨርሲቲ ጋር አብሮ ለመስራት በተደረገው ስምምነት መሠረት ወደ ተግባር ስራ በመገባት የመምህራን የእርስ በእርስ ስልጠና እና ቀጣይ ፕሮጀክት ዙሪያ ሊሰሩ ስለሚገባቸው ስራዎች የስራ አቅጣጫ ተወስዷል፡፡

ከእርስ በእርስ ስልጠናው ከሁለቱ ተቋማት የተወጣጣ ቡድን የተዋቀረ ሲሆን ቡድኑ የቀጣይ ሥራ መነሻ ዕቅድ በፍጥነት እንዲያዘጋጅ የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል የምርምር ክፍል ሃላፊ አቶ ማዘንጊያ ሽመልስ አቅጣጫ ሰጥተዋል፡፡ ፡፡

ከደብረብርሃን ዩንቨርሲቲ የመጡ መምህራን በተቋሙ የሚገኙ የተግባር ስልጠና የሚሰጥባቸውን ክፍሎችም ጎብኝተዋል፡፡

## ተቋሙን ካለበት ደረጃ ከፍ ያደርጋል ተብሎ የታሰበ ሪፎርም እየተሰራ መሆኑ ተገለጸ



የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማስልጠኛ ማዕከል ለተቋማዊ ለውጥ የሚያገለግል ሪፎርም ሥራ በተቋሙ ከፍተኛ ልምድና የትምህርት ዝግጅት ባላቸው መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች እየተዘጋጀ መሆኑ ተገለጸ፡፡

ተቋሙ አሁን ካለበት ደረጃ እንዲያድግና ለውጥ እንዲያመጣ የሪፎርም ሰነድ ማዘጋጀቱ ወሳኝ በመሆኑ ከተቋሙ በተወከሉ ቡድኖች እየተሰራ ያለውን ሥራ የተቋሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተር በቦታው ተገኝተው በጎበኙበት ወቅት ተናግረዋል፡፡

ቡድኑ ለስራው የሚያስፈልጉ የተለያዩ ስልጠናዎችን በመውሰድ ወደ ስራ እንደገቡና ተቋሙ ከአሥር ዓመት በፊት የነበረበትን የተለያዩ ሰነዶች በማንበብ እንዲሁም ከተለያዩ ተቋማት መረጃዎችን በማሰባሰብ አሁን ያለበትን ደረጃ በመለየት ሰነዱን እያዘጋጁ እንደሆነ የቡድኑ ሰብሳቢ ዶ/ር ገብረኪዳን ፍስሃ ተናግረዋል፡፡ ይህ ሰነድ ተዘጋጅቶ ሲያልቅ ተቋሙ አሁን ያለበትን ደረጃ ለማሳደግም ሆነ ለመለወጥ ወሳኝ እንደሆነ ዶ/ር ገ/ኪዳን ገልጸዋል፡፡

## የማሰልጠኛ ማዕከሉ ስድስት ወራት የመማር ማስተማር ሂደት ተገመገመ፡፡



በግምገማው ወቅት በስድስት ወራት ውስጥ የተሰሩ በጎ ስራዎችና ማስተካከያ ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

በዋናነት የተነሱ ነጥቦች የትምህርት ጥራትን በማስጠበቅ ለሀገራችን ቱሪዝም ዘርፍ ብቁ የሰው ኃይል ለማቅረብ የማያስችሉ አሰራሮችን ከወዲሁ መቅረፍ እንደሚገባ እና እርምት የሚያስፈልጋቸው ክፍተቶች ላይ ጠንከር ያሉ እርምጃዎች እንደሚወሰድም የተቋሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ በአጽንኦት ገልጸዋል፡፡

# ከምረቃ ፕሮግራም ፎቶዎች በከፊል የተወሰደ












